በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No ተ/37/ቀ/15/925
ቀን / Date 27/02/2018

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

የገቢ ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ጸድቆ በስራ ላይ የዋለ ቢሆንም የአዋጁ ማስፈጸሚያ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ በመሆኑ በአዋጁ አንዳንድ አንቀጾች ላይ ግልጽነት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ከተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች የተነሱ ጥያቄዎችን በማሰባሰብ በመ/ቤታችን በኩል ለጥያቄዎቹ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጥቅምት 21 ቀን 2018 ዓ.ም በቁጥር 3.0/153/18 በተፃፈ ደብዳቤ የጠየቃችሁትን ይመለከታል።

1. የአማራጭ አነስተኛ ግብር አፈፃፀምን በተመለከተ፤

1.1 ምርት ተረክበው የሚያከፋፍሉ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ ፋብሪካው ወይም አስመጪው የምርቱን የመሸጫ ዋጋ በሚተምንበትና አከፋፋዮቹ የትርፍ ህዳጋቸውን ከፍ/ዝቅ ማድረግ የማይችሉ በሚሆንበት ጊዜ ግብር ከፋዮች ላይ አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚሰላው በኮሚሽኑ ዋጋ ወይም በጠቅላላ ገቢ ላይ ስለመሆኑ፤

ለገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 23 አፈፃፀም በአከፋፋዮች ወይም በጅምላ ሻጭ ነጋዴዎች እና በንግድ ወኪሎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ያስፈልጋል። ለዚህም የግብር ከፋዮቹን የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ ያላቸውን ውል እና ጠቅላላ የሥራ እንቅስቃሴ መመልከት ተገቢ ነው።

ሀ) የንግድ ወኪሎች

የንግድ ወኪሎች ከጅምላ ሻጭ ነጋዴዎች የተለዩና ራሱን የቻለ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጣቸው ሲሆን ሌላኛውን ነጋዴ በመወከል በነጋዴው ስምና ምትክ ውል እንዲዋዋሉ ውክልና የተሰጣቸው ሰዎች መሆናቸው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 2(7) እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ 42 በግልጽ ተመልክቷል። በመሆኑም እነዚህ የንግድ ወኪሎች የዋናውን ነጋዴ ዕቃ በውክልና ተረክበው የሚሸጡ፣ የሸጡበትን ዋጋ ለወካያቸው ገቢ የሚያደርጉ እና ደረሰኝ የሚቆረጠውም በወካዩ ነጋዴ ስም ሲሆን፤ ለወኪሎቹ የሚከፈላቸው የኮሚሽን ክፍያ ብቻ ነው። ስለሆነም የንግድ ወኪሎችን በተመለከተ ለአማራጭ አነስተኛ ግብሩ የሚሰላው በሚያገኙት የኮሚሽን ክፍያ ላይ ብቻ ይሆናል።

ለ) ጅምላ ሻጮች/ አከፋፋዮች

ጅምላ ሻጮች/አከፋፋዮች በስማቸው የማከፋፈል/የጅምላ ንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው፣ ከአምራቹ ወይም ከአስመጪው የቃዎችን ግዢ ፈጽመው ለሌሎች ጅምላ ሻጮች ወይም ቸርቻሪዎች የሚሸጡ፤ በስማቸው ደረሰኝ የሚቆርጡ እና ክፍያ የሚቀበሉ ናቸው። በመርህ ደረጃ ለእነዚህ አይነት ግብር ከፋዮች የአማራጭ አነስተኛ ግብር ማስከፈያ መሰረቱ አመታዊ ጠቅላላ ገቢው ይሆናል፡ ፡ ሆኖም ጅምላ ሻጩ/አከፋፋዩ ከአምራቹ ወይም ከአስመጪው ጋር ባደረገው ውል የገዛቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ለሌሎች ጅምላ ሻጮች ወይም ቸርቻሪዎች የሚሸጥበት ዋጋ እና ጅምላ ሻጩ የሚያገኘው መቶኛ የተወሰነ ከሆነ ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጅምላ መሸጫው



ስልክ 251-11-140 20 00
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24, 55 14 96
251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed-gov.et

ፈ/ክ/ቁ/5/928
27/02/2018

ዋጋ ወይም ጅምላ ሻጩ የሚያገኘው መቶኛ የተወሰነ ከሆነ የአማራጭ አነስተኛ ግብሩ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 23(2(መ) መሰረት በጠቅላላ የሽያጭ ገቢው ላይ ሳይሆን ለጅምላ ሻጩ ከላይ በተጠቀሰው ውል ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል በተፈቀደለት መቶኛ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የድርጅቱ የመሸጫ ዋጋ በውል ወይም በመንግሥት አካል የተወሰነ በመሆኑ አማራጭ አነስተኛ ግብሩ በኮሚሽን ገቢው ላይ እንዲሆን ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅት ይህ ውሳኔ የተላለፈበትን ሕግ ወይም ውል እንደማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 7(2) መሰረት ከላይ ወደ ታች (vertical) ግንኙነት ያላቸው ነጋዴዎች ያላቸው ስምምነት ዝቅተኛ የመልሶ መሸጫ ዋጋን (minimum retail price) የሚወስን ከሆነ የተከለከለ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በአምራች ወይም በአስመጪው እና በጅምላ ሻጭ/በአከፋፋይ መካከል የሚደረገው ውል የጅምላ መሸጫ ዋጋን እንጂ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን የሚወስን ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ከሚወሰን የችርቻሮ መሸጫ ውጪ (ለምሳሌ ነዳጅ) በችርቻሮ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች የመሸጫ ዋጋ በውል ተወስኗል የሚል ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

በሌላ በኩል ጅምላ ሻጩ/አከፋፋዩ ከአምራቹ ጋር የገባው ውል ወይም በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ውሳኔ የዕቃ እና አገልግሎት የጅምላ መሸጫ ዋጋን እና ጅምላ ሻጩ የሚያገኘውን መቶኛ የሚወስን ድንጋጌን ያላካተተ ከሆነ አከፋፋዩ ከመሸጫ ቦታ፣ ከገዥው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ከጊዜ እና ከሌሎች መነሻዎች የማከፋፈያ ዋጋውን የመወሰን ነፃነት ያለው በመሆኑ አማራጭ አነስተኛ ግብሩ የሚሰላው ከአመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ ይሆናል፡፡

## 1.2 የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን ከአባላት በመውሰድ አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራትን በተመለከተ፤

ማህበሩ እና አባላቱ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በመሆናቸው አስቀድሞ የተወሰነ መቶኛ ክፍያ ብቻ ለማህበሩ እንዲከፈል በማድረግ ቀሪውን አባላት እንዲከፈላቸው መደረጉ የትክክለኛ የገበያ ዋጋ መርህን የተከተለ ስለመሆኑ ተገቢው ፍተሻ ሊደረግበት የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለታክስ ሕግ አላማ ማህበሩ እና አባላቱ የሚያከናውኑት ግብይት ሁለት ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ከሚያከናውኑት የኪራይ አገልግሎት አንጻር መታየት ይኖርበታል፡፡

ማህበሩ ተሽከርካሪዎቹን አባል ካልሆኑ ሰዎች ቢከራይ እና ክፍያ ቢፈጽም የኪራዩ ገቢ አመታዊ ጠቅላል ገቢ ውስጥ የሚካተተ በመሆኑ በተመሳሳይ ማህበሩ ከአሰሪዎች የተከፈለው ክፍያ በተናጠል የሚታይ እና በአመታዊ ጠቅላላ ገቢው ውስጥ መካተት የሚገባው ነው፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን ማህበሩ ከአሰሪዎች ከሚከፈለው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 3 በመቶ ብቻ በመቁረጥ ቀሪውን ገንዘብ ለተሽከርካሪው ባለቤት ለሆነው አባል የሚሰጥ ቢሆንም፤ ማህበሩ የተቀበለው ገንዘብ መጠን አመታዊ ጠቅላላ ገቢ ስሌት ውስጥ ተካቶ ለአማራጭ አነስተኛ ግብር መሰረት ይሆናል፡፡

## 1.3 በሜትር ታክሲ የመተግበሪያ አቅራቢዎችን ጨምሮ የኮሚሽን ገቢ/የአገልግሎት ገቢ የሚያገኙትን በተመለከተ፤

በአዋጁ አንቀጽ 23(8(ሐ)) ኮሚሽን ለሚለው ቃል በህግ ወይም በተዋዋይ ወገኖች መካከል በተደረገ ውል በተወሰነው መሰረት ከአንድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ላይ ለአገልግሎት ሰጪው የሚከፈል ገንዘብ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ኮሚሽን የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በአዋጁ አንቀጽ 8 (2(መ))

ዋጋቸው በውል ወይም በመንግሥት አካል የተወሰነ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ድርጅትን በሚመለከት ሲሆን አማራጭ አነስተኛ ግብር መጣኔው ተፈፃሚ የሚሆንበት መሰረቱ የሚከፈለው ኮሚሽን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

የሜትር ታክሲ የመተግበሪያ አቅራቢዎችን ጨምሮ የኮሚሽን ገቢ/የአገልግሎት ክፍያ የሚያገኙ ግብር ከፋዮች በግብር ዓመቱ ላከናወኑት አገልግሎት የመስጠት ተግባር ያገኙት ገቢ ኮሚሽን ወይም የአገልግሎት ክፍያ በሚሆንበት ወቅት እና ይህም ባቀረቡት የሂሳብ መዝገብ ላይ የሚታይ ከሆነ በአዋጁ የተሰጠውን የዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ ትርጉም የሚያሟላ ነው፡፡

ስለሆነም ለአማራጭ አነስተኛ ግብር ክፍያ መሰረት የሚሆነው ጠቅላላ ዓመታዊ የኮሚሽን ወይም የአገልግሎት ገቢው ይሆናል፡፡

## 1.4 ከሐምሌ 1 ቀን 2017 በፊት የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቅ የማይገደዱ ሰዎች ላይ አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈጻሚነትን በተመለከተ፤

የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከገቢ ግብር ነፃ ተደርገው የነበሩ እና በማሻሻያ አዋጁ የገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ግዴታ የተጣለባቸውን ሰዎች በተመለከተ የገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ተፈጻሚ የሚሆነው ሕጉ ተፈጻሚ ከሚሆንበት የታክስ ዓመት በኋላ ላለው ገቢ ይሆናል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 4(1) መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈፃሚ የሚሆነው ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በሚሰበሰብ ግብር ላይ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከሐምሌ 1 ቀን በፊት ላለው ጊዜ ከንግድ ትርፍ ግብር ነጻ የነበሩ ሰዎች ላይ ሊሰበሰብ የሚችል ግብር የሌለ በመሆኑ ለ2017 የታክስ አመት አማራጭ አነስተኛ ግብር እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡

በተጨማሪም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፍ ግብር እንዲከፍሉ የሚገደዱት ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በሚያገኙት የንግድ ትርፍ ገቢ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ በተሻሻለው የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 89(5) መሰረት ለመጀመሪያው የግብር አመት አመታዊ ግብር የሚከፍሉት ዓመታዊ ገቢያቸውን ማስታወቅ ባለባቸው ጊዜ ይሆናል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ግብር ከፋዮች ለ2018 ግብር ዓመት በየሶስት ወሩ የሚከፈለው ቅድሚያ ግብር የሚመለከታቸው አይሆንም፡፡

## 1.5ሂሳባቸውን መጋቢት ወይም ሚያዝያ የሚዘጉ ድርጅቶች አማራጭ አነስተኛ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ

በአዋጁ አንቀጽ 4(1) መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈፃሚ የሚሆነው ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በሚሰበሰብ ግብር ላይ እንደሚሆን በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለአማራጭ አነስተኛ ግብሩ አፈጻጸም መታየት ያለበት ግብር ከፋዩ ሂሳብ የሚዘጋበት ወቅት ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት መሆኑ ሳይሆን ግብር ከፋዩ ግብሩን የከፈለበት ወቅት ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም በኋላ ባለው ጊዜ መሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም ግብር ከፋዮች ሂሳባቸውን መጋቢት ወይም ሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም በመዝጋት ግብራቸውን አሳውቀው የከፈሉት ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም በኋላ ከሆነ የአማራጭ አነስተኛ ግብሩን የመክፈል ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## 1.6 ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ የተደረጉትን ዕዳ በማሸጋሸግ እና በኪሳራ ምክንያት በመፍረስ ያሉ ድርጅቶች በተመለከተ፤

በአዋጁ አንቀጽ 23(6) መሰረት በኪሳራ ምክንያት በመፍረስ ላይ ያለ እና በእዳ ማሸጋሸግ ላይ ያለ ድርጅት ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነፃ እንደሚሆን ተመልክቷል። እነዚህ ሁለት የህግ ጽንሰ ሃሳቦች መታየት ያለባቸው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 588 እስከ 825 ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ስለማዋቀር፣ መልሶ ማደራጀት እና የመክሰር ሕግን በተመለከተው ማዕቀፍ ስር ነው።

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181(5) አንድ ድርጅት በኪሳራ ምክንያት ሊፈርስ የሚችለው ድርጅቱ ስለመክሰሩ በፍርድ ቤት ሲወሰን መሆኑ በተደነገገው መሰረት አንድ ድርጅት በኪሳራ ምክንያት እየፈረሰ በመሆኑ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነፃ ሊደረግ የሚችለው ኪሳራው በፍርድ ቤት የተወሰነ ሲሆን እና ይህን የሚያስረዳ ሰነድ ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል።

በሌላ በኩል የዕዳ ማሸጋሸግን በተመለከተ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 635 እስከ 704 በተደነገገው መሰረት ግብር ከፋዩ መወጣት የማይችለው የገንዘብ ችግር ያገጠመው መሆኑ ሲረጋገጥ እና ለፍርድ ቤት ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ የመልሶ ማደራጀት ሥነ ሥርዓት የሚከፈት ይሆናል። በመሆኑም ግብር ከፋዩ በዕዳ ማሸጋሸግ ላይ ያለ በመሆኑ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የዕዳን መልሶ ማደራጀት ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ያቀረበበትን ማመልከቻ፣ በባለገንዘብ ኮሚቴ የጸደቀበትን ማስረጃ ወይም ፍርድ ቤት የመልሶ ማደራጀቱ እንዲከናወን የወሰነበትን ውሳኔ ለታክስ ባለስልጣኑ በማቅረብ ይሆናል።

በመሆኑም ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ውጭ ተበዳሪዎች ከፋይናንስ ተቋማት የወሰዱትን ብድር መክፈል ባለመቻላቸው የተወሰነ እፎይታ ሲሰጣቸው እና እዳቸውን ለመክፈል አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲችሉ የሚገቡት የክፍያ ዘመን፣ የወለድ መጠን፣ የአከፋፈል ሥርዓት እና ተመሳሳይ የዕዳ ሽግሽግ ግብር ከፋዩ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነፃ እንዲሆን የሚያስችል አይደለም።

## 1.7 ለአማራጭ አነስተኛ ግብር መነሻ ሊሆን የሚችል መረጃ በማይገኝበት ወቅት ግብሩ ተግባራዊ ስለሚደረግበት አግባብ፤

አማራጭ አነስተኛ ግብሩን ተፈፃሚ ለማድረግ የታክስ ባለስልጣኑ የግብር ከፋዩን አመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ሊያውቅ ይገባል። ግብር ከፋዩ እነዚህን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ማቅረብ የማይችል ከሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት የታክስ ባለስልጣኑ የሽያጭ ገቢውን በግምት ሊወስን ይችላል።

በመሆኑም የግብር ከፋዩ ጠቅላላ ገቢ በግምት የሚወሰንባቸውን በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተመለከቱ ዘዴዎች በመጠቀም የሽያጩ ገቢ በግምት መወሰን ይኖርበታል።

## 2. ቀደም ሲል በሌላ ህግ ነጻ የተደረጉ ግብር ከፋዮች የ2017 በጀት አመት የንግድ ትርፍ ግብር ተጠያቂነትን በተመለከተ፤

በአዋጁ አንቀጽ 4(1እና2) ከተደነገጉት የክፍያ ስርአቶች በስተቀር በአዋጁ የተደረጉ ሌሎች ማሻሻያዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ መሆኑ በአዋጁ ተደንግጓል። ስለሆነም ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት የተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የገቢ ግብር አዋጅ ከመሻሻሉ በፊት የነበሩት ድንጋጌዎች ናቸው።

በመሆኑም ቀደም ሲል በሌላ ህግ ከገቢ ግብር ነጻ የተደረጉ ግብር ከፋዮች ከግብር ነጻ በነበረው ገቢ ላይ በ2017 የግብር አመት የንግድ ትርፍ ግብር አስታውቀው እንዲከፍሉ አይገደዱም። ነገር ግን እነዚህ ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በሚያገኙት ገቢ ላይ በአዲሱ አዋጅ

መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነድ እና መንግስት ባወጣቸው ቦንዶች ላይ ከሐምሌ 1 ቀን 2017 በፊት የተገኙ ገቢዎች ላይ የማሻሻያ አዋጁ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 3. የትርፍ ድርሻ ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆን ታክስ

በዲቪደንድ (በትርፍ ድርሻ) ገቢ ላይ የአዋጁ ማስከፈያ መጣኔ ወደ 15 በመቶ ከፍ የተደረገው ከነሀሴ 1 ቀን 2017 ጀምሮ በሚሰበሰብ የዲቪደንድ ግብር ላይ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 57 መሰረት የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻን በተመለከተ የማከፋፈል ውሳኔው የተሰጠው ከነሀሴ 1 ቀን 2017 በኋላ ከሆነ ግብሩ የሚከፈለው በአዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በ2016 በፊት ከተገኘ የተጣራ ትርፍ ላይ ድርጅቱ በ2017 በጀት አመት በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ትርፉን ለአክሲዮን ባለቤቶች ማከፋፈል ወይም ካፒታል ለማሳደግ ማዋል ያለበት ሲሆን፣ ከሁለት አንዱ ውሳኔ ያልተሰጠበት ትርፍ ካለው የ12 ወራት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት 2 ወራት ውስጥ ባልተከፋፈል ትርፍ ላይ የሚከፈለው ግብር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ ያልተከፋፈለው ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፍል የሚገደደው 12ኛው ወር ካለፈ በኋላ ካለው ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የ12 ወር ጊዜ የሚያርፈው ከነሀሴ 1 ቀን 2017 በኋላ ከሆነ በተሻሻለው አዋጅ በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ መሰረት ይስተናገዳል፡፡

በመሆኑም የትርፍ ድርሻ እና ያልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው 15 በመቶ መጣኔ ተፈጻሚ የሚሆነው ግብሩን የመክፈል ግዴታ የሚጀምርበት ቀን ከነሀሴ 1 ቀን 2017 በኋላ ባለው ጊዜ ከሆነ ነው፡፡

## 4. የተጠቃለለ የሂሳብ ሰነድ ተግባራዊ ስለሚደረግበት አግባብ፤

በገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ አንቀጽ 86(7) በሰንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት እና ከአንድ በላይ ከሆነ የንግድ ሥራ መስክ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ለእያንዳንዱ የተለየ የሥራ መስክ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ መረጃዎችን በተናጠል መያዝ ያለበት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የተቀረፀው፣ ግልጽነት በጎደለው የሂሳብ ማጠቃለል (consolidation) ምክንያት ግብር የሚከፈልበት ገቢ እንዳይዛባ በመከላከል፣ የግብር ስሌትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ አይነቱ መለያየት ከሌለ፣ ከአትራፊ የንግድ መስክ የተገኘን ትርፍ በሌላኛው መስክ ከተገኘ ኪሳራ ጋር በማቻቻል የግብር መሰረቱ ሊሸረሸር ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተው የሂሳብ ሰነዶችን በተናጠል የመያዝ ግዴታ የአማራጭ አነስተኛ ግብር በሚወሰንበትም ወቅት ሥራ ላይ ይውላል፡፡ በመሆኑም ለአማራጭ አነስተኛ ግብር ማስከፈያ መሰረት የሆነው አመታዊ ጠቅላላ ገቢ እና ሊከፈል የሚገባው ግብር መታየት ያለበት በእያንዳንዱ የንግድ ሥራ መስክ የሚቀርቡ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ ሰነዶችን መሰረት በማድረግ ሊሆን ይገባዋል፡
:

ይሁን እንጂ ከዚህ በላይ የተመላከተው የአዋጁ ማሻሻያ ተፈፃሚ የሚሆነው ከሀምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የተገኘ ገቢ ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ግብር ከፋዮች የ2017 ዓ.ም የንግድ ትርፍ ግብርን በሚያሳውቁበት ወቅት ለተሰማሩበት እያንዳንዱ የንግድ ሥራ መስክ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ ሰነዶችን በተናጠል እንዲይዙ አይገደዱም፡፡

## 5. የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ላይ አማራጭ አነስተኛ ግብር እና የቅድሚያ ታክስ ክፍያ የሚኖረው ተፈፃሚነት

በአዋጁ አንቀጽ 23(1) የተጣለው አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚሰላው ግብር ከፋዩ በግብር አመቱ ከተለያዩ የንግድ ሥራ ገቢ ምንጮች ባገኘው ትርፍ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ግብር ከጠቅላላ አመታዊ ገቢው ጋር ሲነፃፀር ከ2.5 በመቶ በታች ሲሆን ነው። ከንግድ ሥራ ገቢ የሚገኝ ትርፍ ላይ ግብር የሚከፈለው ደግሞ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት በመሆኑ አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈፃሚ የሚሆነው በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት በሚከፈል የንግድ ትርፍ ግብር ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም በሰንጠረዥ "ለ" የተካተተው የቤት ኪራይ ገቢ ላይ አማራጭ አነስተኛ ገቢ ግብር ተፈፃሚ አይደረግበትም።

በሌላ በኩል በአዋጁ አንቀጽ 89(2እና4) መሰረት የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች የተቀመጠውን የመክፈያ ጊዜ መሰረት በማድረግ ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር 25% (ሃያ አምስት) በመቶ በየሦስቱ ወሩ አስቀድመው የመክፈል ግዴታ አለባቸው። በማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ 3 የተቀመጡት ሁለት የግብር ከፋይ ደረጃዎች (ደረጃ 'ሀ' እና 'ለ') ምድብ ተፈፃሚ የሚሆነው ለንግድ እና ለኪራይ ገቢ ግብር ዓላማ ነው። ስለዚህ በአዋጁ አንቀጽ 89(2እና4) የተቀመጠው በየሦስቱ ወሩ የሚከፈለው የ25% (ሃያ አምስት) በመቶ የቅድሚያ ታክስ ክፍያ የቤት ኪራይ ገቢ ላይ ጭምር ተፈፃሚ ይሆናል።

## 6. አማራጭ አነስተኛ ግብር እና የገቢ ግብር እፎይታ፡

በአዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ በኢንቨስትመንት ህግ የግብር እፎይታ በተሰጠው ሰው ላይ አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈጻሚ እንደሚሆንና አማራጭ አነስተኛ ግብሩ የሚሰላው የተሰጠው ማበረታቻ ተቀናሽ ተደርጎ ሊከፈል በሚገባው የገቢ ግብር ላይ እንደሚሆን ይደነግጋል።

በሥራ ላይ ባለው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሕግ የገቢ ግብር እፎይታ የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች መብቱ ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ የንግድ ትርፍ ግብር እንዲከፍሉ አይጠበቅባቸውም። የማሻሻያ አዋጁ ታሳቢ ያደረገው አዲስ በሚወጣው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ መሰረት ማበረታቻ ለተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ተፈጻሚ የሚሆነውን ከመደበኛው የማስከፈያ መጣኔ አነስ ያለ የማስከፈያ መጣኔ ነው።

በመሆኑም በሥራ ላይ ፀንቶ በሚገኘው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሕግ መሰረት የገቢ ግብር ነፃ መብት የተሰጣቸው ኢንቨስተሮች ላይ አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈፃሚ አይደረግም።

## 7. ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እና የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድን በተመለከተ፤

ድርጅቶቹ ለአባላቶቹ በየአመቱ መጨረሻ ያከፋፈሏቸውን ትርፍ ለታክስ ባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ የተጣለባቸው ስለሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና ግብርን መክፈልን በተመለከተ ያለባቸውን ግዴታ ባለመወጣት የሚከፈል ቅጣት እና ወለድ ተፈፃሚ ይሆንባቸዋል። እንዲሁም ድርጅቶቹ የሚያቀርቧቸውን የሂሳብ ሰነዶች እና የሚከፈሉ ታክሶችን በተመለከተ ስለትክክለኝነታቸው የታክስ ባለስልጣኑ ተገቢውን መደበኛ ኦዲት እና ማጣራት ሊያደርግ ይገባል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ድርጅቶች የሚከፍሉት የንግድ ትርፍ ግብር ባለመኖሩ ኪሳራ ቢያጋጥማቸው የኪሳራ ማሸጋገር ተጠቃሚ አይሆኑም።

በተጨማሪም ድርጅቶቹ ለሚገዙት የዕቃ እና አገልግሎት አቅርቦት የዊዝሆልዲንግ ታክስ የመሰብሰብ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን፤ ድርጅቶቹ የሚያገኙት ገቢ ከግብር ነጻ የተደረገ በመሆኑ ከሚሰጡት አገልግሎት ላይ ክፍያ ሲቀበሉ የዊዝሆልዲንግ ታክስ ተቀናሽ አይደረግባቸውም።

8. የጥሬ ገንዘብ ግብይት ገደብን በተመለከተ፡

ከ50 (ሃምሳ) ሺህ ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ የተገበያዩ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ የተቀመጠው ገደብ በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት በመሆኑ ተፈፃሚ የሚሆነው ለገቢ ግብር ብቻ ይሆናል። በመሆኑም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት የተፈቀደውን የግብዓት ታክስ የማቀናነስ መብት የሚገድብ አይሆንም።

በአዋጁ አንቀጽ 29 (1(ኘ) መሰረት ገቸው ግብር ከፋይ ከ50 (ሃምሳ) ሺህ ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ የከፈለ እንደሆነ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ የተከፈለው ክፍያ የንግድ ትርፍ ግብር በሚሰላበት ወቅት እንደተቀናሽ ወጪ ሊያዝ አይገባም።

በሌላ በኩል ሻጩ ግብር ከፋይ ከ50 (ሃምሳ) ሺህ ብር በላይ በትርፍ የተቀበለውን ጥሬ ገንዘብ እኩል የገንዘብ ቅጣት የሚከፍል መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 88 ተደንግጓል። ቅጣቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተቀበለው ግብር ከፋይ በአንድ ቀን ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር በተደረገ ጠቅላላ ግብይት፣ ወይም ከአንድ ግብይት ጋር በተያያዘ የፈጸመው ክፍያ፣ ወይም ከአንድ ሰው ጋር ከተፈጸመ አንድ ግብይት ወይም ተግባር ጋር የተያያዘው ክፍያ ከ50 ሺህ ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ የተቀበለ ከሆነ ነው። በመሆኑም ሊታይ የሚገባው በአንድ ተናጠል ግብይት ግብር ከፋዩ የተቀበለው በደረሰኝ ላይ የሰፈረው መጠን ብቻ ሳይሆን በአንቀጽ 81(1) የተዘረዘሩትን ግብይቶችን ከግምት በማስገባት ነው።

ከአንድ በላይ ንዑስ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸውን ግብር ከፋዮች በተመለከተ የጥሬ ገንዘብ ግብይት ላይ የተደረገው ገደብ ተፈፃሚ የሚሆነው እያንዳንዱን ንዑስ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ራሱን እንደቻለ አንድ ግብር ከፋይ በመቁጠር ይሆናል።

9. የተርን ኦቨር ታክስ አዋጁ መሻርን በተመለከተ፤

በአዋጁ አንቀጽ 3 መሰረት የተርንኦቨር ታክስ አዋጅ ተፈፃሚ ሆኖ የሚቀጥለው አዋጁ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ዓመት በፊት ያልተሰበሰበ ግብርን በተመለከተ ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል። የገቢ ግብር አዋጅ ጸድቆ ከመውጣቱ በፊት አስቀድሞ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሰረት ሽያጭ ወይም የአቅርቦት ስምምነት ተደርጎ አቅርቦቱም የተጠናቀቀ ከሆነ በግብይቱ ላይ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጁ ተፈፃሚ ይሆናል።

ይሁን እንጂ ውሉ የተፈጸመው የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ከመሻሩ በፊት ቢሆንም የተርን ኦቨር ታክስ ከተሻረ በኋላ በውሉ መሰረት በሚፈጸም አቅርቦት ላይ የሚሰበሰብ የተርንኦቨር ታክስ አይኖርም።

ምንም እንኳን ስምምነቱ በተደረገበት ወቅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ባይሆንም እንዲህ አይነት ለውጦች ሊታዩ የሚገባው በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንቡ አንቀጽ 37 እና 38 በተደነገገው አግባብ ነው።

በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ አንቀጽ 36 ማናቸውም የእቃ ወይም የአገልግሎት ማቅረብ ውል የፈረመ ታክስ ከፋይ ውሉን ከፈረመ በኋላ በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተጣለ ለአቅርቦቱ ከሚከፈለው ዋጋ በተጨማሪ የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከአቅርቦት ተቀባዩ ሊጠይቅ እንደሚችል ተደንግጓል። በመሆኑም የተርንኦቨር ታክስ ከፋይ የነበረ አቅራቢ ለተጨማሪ

እሴት ታክስ እንዲመዘገብ ከተደረገ አስቀድሞ በፈረመው ውል መሰረት በሚያቀርበው እቃ ወይም አገልግሎት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ ይኖርበታል።

ሆኖም ታክስ ከፋዩ የደረጃ "ለ" ታክስ ከፋይ ሆኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት ከሆነ የተርንኦቨር ታክስ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ የተርን ኦቨር ታክስ ሊሰበስብ አይችልም።

በሌላ በኩል የተር ኦቨር ታክስን የሻረው የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ በሁሉም ክልሎች ጸድቆ ስራ ላይ የዋለ በመሆኑ በክልል መንግስታትም የተርንኦቨር ታክስ አዋጅ ተሽሯል። በመሆኑም የክልል ግብር ከፋይ በሆኑ ግለሰብ ግብር ከፋዮች የሚሰበሰብ የተርንኦቨር ታክስ ሊኖር አይችልም።

የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጁ ተፈፃሚ ከሆነበት የገቢ ግብር ዓመት በፊት እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1104/2017 ካስቀመጠው የአንድ ወር (መስከረም 27) ቀን በፊት የተቆረጡ የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኞች እና የተከፈሉ የታክሱ ክፍያዎች ለወጪ መያዣነት ሊያዙ ይገባል። ለታክስ ባለስልጣኑ ያልተከፈሉ የታክስ ክፍያዎች የተሻረው አዋጅ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መክፈል ያለባቸው ሲሆን፣ ይህንን መተላለፍ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ቅጣት እና ወለድ የሚጠየቅባቸው ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት የተሻረውን የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ በመጠቀም የሚሰበሰብ ታክስ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ማንኛውም ሰው የተርን ኦቨር ታክስን የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 127 መሰረት የወንጀል ቅጣት ተጠያቂ ሊደረግ ይገባዋል። ሆኖም በዚህ መልኩ የተርን ኦቨር ታክስ የሰበሰበው እና ደረሰኝ የቆረጠው ግብር ከፋይ የሰበሰበውን ታክስ ለባለስልጣኑ አስታውቆ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል። በሌላ በኩል ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ የተቀበለው ግብር ከፋይ ለዚህ ግብይት የከፈለው ክፍያ በወጪነት ሊያዝለት አይገባም።

ስለዚህ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከዚህ በላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር